

# ለምድራዊው
# አለም የተላከ
# የዘላለማዊው አባት
# የመንፈስ መልዕክት



## የሁለንታ ሳይንስ

## በአልፋ እና ኦሜጋ

# የእግዚአብሄር ነገር ለማንም ለብቻው የተሰጠ አይደለም




ይህ ጥቅልል telepathic ስፓኒሽ የተጻፈው (1975-1978 ሊማ, ፔሩ)



## ለምድራዊው አለም የተላከ የዘላለማዊው አባት የመንፈስ መልዕክት፣ ሁለተኛ ክፍል፣ የመጀመሪያው መልዕክት ከአለም ተነጥሎ በሀይማኖት አለት ውስጥ የተደበቀ፡፡

አወ ልጆቸ፣ አንዱ የሚወለድ እውነትን ፍለጋ ነው፤ የሚያነሳሳውም የእውቀቱ አለም ነው፤ ራዕዩም ለብዙ ክፍለ ዘመናት ሲጠበቅ ኑሯል፡፡ ፈጣሪያቸሁ ህያው ዶግማዎቸን ለአለማት ግስጋሴ ይጠቀማል፤ ባለፉት ጊዜያት የሙሴ ህግን ላከ፣ በመቀጠልም የክርስትናን ዶግማ፣ በሶስተኛነትም እየተነሳ ያለው የአምላክ በግ ዶግማ ወይም ደግሞ በሌላ መጠሪያው የሁለንታ ሳይንስ ዶግማ ይባላል፡፡ መሰረቱ የሚያርፈውም እንደ ተፈጥሮ በሆነ ባህርይ ላይ ነው፡፡ በመንፈስ

የተቀደሰው ፅሁፍም ከአለማት ፈጣሪ ጋር እንደመገናኛ የሚጠቀመው ነው፤ ሁሌም ደግሞ እንደዚህ ነበር፣ ባለፉት ጊዜያት ነብያት ዶግማን የሚቀበሉት በመንፈስ ነበር፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ነገር መሰረት ያለውና ለህልውናም መንስኤ የሆነ  ነው፡፡ የአምላክ በግ ዶግማም መጨረሻ የሌለው ነው፡፡ ይሀውም በአለማት የሌለ ስለሆነ  ነው፤ እንዲሁም በተመሳሳይ ምክንያት በመላው አለም ላይ ይሰራጫል፤ ወደ አለም ቋንቋዎች ሁሉ የሚተረጎም ይሆናል፤ በሚያመጣው ተፅዕኖም በዝባዡን ቁሳዊነት እንዲወድቅ ያደርጋል፣ ምክንያቱም አዲስ የሆነን ስነምግባር ወደ አለም ያመጣል፣ ለሺህ ዘመን ሰላም የሚስማማ ስነ ምግባር፡፡ የዘላለማዊው አባት ዶግማ ሁሌም አለምን የሚያድስ ነው፤ ልክ ከዚህ ቀደም እንደሆነው ሁሉ፤ አዲሱ ራዕይም በአሁኖቹ የሰው ልጅ መንፈስ የተጠየቀ ነው፣ እናም ለእናንተ ተሰጥቷቿኋል፤ በህልውናቿን

እያንዳንዷ የምንኖራት ቀጽበትም የጠየቅነው እና የተቀበልነው ነው፡፡ ይህ አዲሱ ራዕይም የተቀደሱ ጽሁፎች ቅጣያ ሲሆን፤ አንዱ የቅዱስ ጽሁፎች የሚተንትን ሲሆን ሌላው ደግሞ ሀይማኖታዊ ነው፤ የመጀመሪያው ዘላለማዊ ነው ምክንያቱም ሁልጊዜም መንፈሳችሁ መሰረቷን ትፈልጋለችና ነው፤ ሁለተኛው የእምነት መነገጃው ነው፤ ከአለም ቀድመው የሚወቀሱት ሀይማኖቶች ናቸው፤ በአምላክ በግ ዶግማ መሰረት ሀይማኖቶች በስዕብና ላይ የአለምን እምነት ከፋፍለዋል፣ ይሄን የማድረግ አንዳንች እንኳ መብት የላቸውም፤ አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ ረስተዋል፤ አንድ እውነት ብቻ እንዳለ ረስተዋል፤ ሰይጣን ብቻ ነው ራሱንም ሆነ ሌሎችን የሚከፋፍል፡፡ የሀይማኖት መንፈሶች በሮም ዘመን እንደነበሩት ጥንታዊ አይሁዶች አይነት ናቸው፤ ያለፍትን ጊዜያት ሀጢያት ያነጻ ዘንድ አምላክን ዳግመኛ እንዲወለድ ጠየቁት፤ ፍርዱም በእነርሱ ላይ ሆነ፤

በአለም ያሉት ሁሉም ሀይማኖተኛ ሰወች መርሳት የሌለባቸው ነገር፤ እያንዳንዱ መንፈስ ራሱ በመረጠው እጣ ፈንታ ለፍርድ የሚቀርብ ነው:: የአለቱ መንፈሳችሁ በአጽናፍ አለምም ተመሳሳይ ድርጊት ያደርጋል፤ ሌላውን መንጋ ትከፋፍላላችሁ፤ በሌሎች ፍጥረታት ላይ መንፈሳዊ ውዝግብን ትነዛላችሁ፤ ብዙዎቹን ፕላኔቶች በቁሳዊ ምኩራቦች ሞላችሁ፤ ይህንንም በምድር ላይ ዳግመኛ አደረጋችሁት፤ ይሀውም በመጀመሪያ እንድትዳኙ ያደርጋችኋል፤ ህግጋቱንም በመተላለፍ ቀዋሚ_ክርስቶስ ሆናችሁ፤ እያንዳንዱ ትዕዛዛቱን የሚተላለፍ ሁሉም እንዲህ ሆነ ማለት ነው:: እናንተም የቅድስት እናታችን ቤተ ክርስቲያን ትላላችሁ፤ እኔም እላችኋለሁ በዚህ አለም ማንም ፃድቅ ወይም ቅዱስ አይደለም፤ እውነተኛ ትህትና በመንግስተ ሰማይ የማይታወቅ ማዕረግን አይፈልግም፣ የናንተው ደቂቋ ፕላኔትም እንዲሁ፣ ከአንድ አባት እና ከአንዳንድ ነብያት በቀር ይህች

ትቢያ ፕላኔት መሬት እንደሆነች አያውቁም፤ የዚህ ምክንያትም የአባት ጆሻ የመኖሪያ ውኖች ማብቂያ የላቸውምና ነው፤ እንዲሁ ማንስ እንኳ ትልቅ ቢያስብ አይሆንለትም:: ለእናንተም ብልግና የሚል ቃል ተጻፈ፤ ምክንያቱም በእኔ መለኮታዊ ህግ ትነግዳላችሁ፤ እውራን ሌሎች እውራንን ይመራሉ፤ የራሳችሁን ስህተት ለሌሎች እውራን ታስተላልፋላችሁ፤ አዲሱ ዶግማ ሲሰራጭም፣ የእናንተ መንፈሳዊ ራስ ወዳድነት ይከፋፈላል፤ አለት የሚለው ቃል የምንም ነገርን ዘላለማዊነት አይወክልም፤ ምድርም አንፃራዊ እንጂ ዘላለማዊ አይደለችም:: እናንተ ቤተ ክርስቲያናችሁ ዘላለማዊ እንደሆነች ታስባላችሁ፣ የሚመጡት ክስተቶች ከዚህ ስህተት የሚያወጧችሁ ይሆናል:: በልባቸው ትሁት ያልሆኑት ብቻ ዘላለማዊነትን ያገኛሉ፤ እነዚያ ከስነ ምግባር የወጡ ግን ስነ ምግባርን የሚያስተምሩት ግን አይቻላቸውም:: የመጀመሪያ ልጄ በፊት በምድር ላይ እንዳለው፤

በዚህ አለት ቤተ ክርስቲያኔን እተክላለሁ ማለቱ የሰውን ልጅ ወደፊት ተመልክቶ ነው፤ የጸሀዩ ሶስትነትም ሁሉም ጋ ያለ ነው፤ እንዲሁ ደግሞ በምንኖረው ጊዜ ያለ ነው፤ ያለፈው፣ የአሁኑ፣ የወደፊቱ፤ እናም ምን ተመለከተ? ሁሉንም መተላለፋችሁ ተመለከተ፣ ምስኪን ፍጡራንን ስትጨቁኑ ተመለከተ፤ ምክንያታችሁም ሀሳባችሁን ስላልተጋሯችሁ ነው፤ ምድራዊያንንም እንዳነገሳችሁ ተመለከተ፣ የምኞታችሁ አለት አንድ ብቻ የንጉሶች ንጉስ መለኮታዊ አባት፤ ህይወትን የሚሰጥም ሆነ የሚነሳ፤ ንጉስ የሚለው ማዕረግም ከውኖች አለም የሆነ ነው፣ ሰይጣንም የርኩስ መንፈስ ንጉስ ይባላል፡፡ ትዕዛዛቱም ንጉስ እንድንሆን አያስተምሩንም፣ ግን ከምንም በላይ ትሁት እንሆን ዘንድ ያስተምሩናል፡፡ የአባት ልጆች የሚገዳደሉበትን መሳሪያ እንዴት እንደምትባርኩ ተመለከት፤ ሰይጣናትንም አውቆ በመለኮታዊ ትዕዛዛቱ

እናንተ መግደል አትችሉም አላቸው:: በእምነት ላይ የሚነግዱትንም ተመለከተ:: እንዲሁ በመንፈሳቸሁ ያለውን ኢ_ስነምግባራዊነት ተመለከተ፤ ህግጋቱንም ዳግመኛ ከመተላለፍ ይልቅ ዳግመኛ እንዳይወለድ አለመጠየቅ የተሻለ ነበር:: የእናንተ ሀይማኖትም በመንግስተ ሰማይ ዘንድ የማይታወቅ ነው:: እንዲሁም የአባትን ልጆቸ እምነት የሚከፋፍል ስነምግባር የማይታወቅ ነው፣ በመንግስቱ የሚታወቀው ብቸኛው ምኩራብ ስራ ነው፣ ስራ ይህቸ ደቂቋ ፕላኔት ከመወለዷ በፊት የነበረ ጥንታዊ እና እስካሁን ያለ ግዴታ ነው:: ስራ በግዙፍ አለማት እንኳ የነበረና ያለ ነው:: የስራ ምኩራብም ወደ ትቢያነት ተቀይሮ አያውቅም፣ የእናንተ ቁሳዊ ምኩራብ ግን ወደ ትቢያነት ይለወጣል እንዲሁ በፕላኔት ያለ ቁሳዊ መዋብም፤ ይሄውም መታሰብ እንኳ ያልነበረበት መዋብ ነበር:: ምክንያቱም ይህ መዋብ መሰረቱን ግብዝነት ላይ ስላደረገ የአለምን ግስጋሴ

በመንፈሳዊነትም ሆነ በስነ ምግባራዊነት በሀያ ክፍለ ዘመን እንዲዘገይ አድርጎታል፡፡



አወ ትንሹ ልጄ፣ ይህ ሰማያዊ ገለጻ የሚያሳየው እያንዳንዱ ፍትህ የሚመጣው ፍጥረታት እንደሚራቡበት ባለው ተመሳሳይ መንገድ ነው፡፡ ሁሉም የሰው ልጅ መንፈስ ይህን ፍትህ በመንግስተ ሰማይ ተመልክተውታል፣ ምክንያቱም ሁሉም የራሱን ፍትሀዊነት ይመለከት ዘንድ ተሰጥቶታልና ነው፡፡ ማንኛውም ነገር በመንግስተ ሰማይ ዘንድ ይገኛል፤ ማንም ወደዚህ አለም በመንፈስ ታውሮ አይመጣም፣ በግብራችን ልክ

ፍትህ አለ፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ የራሳቸው ገነት ይኖራቸው ዘንድ ቃል ተገብቶላቸዋል፤ በህልው ትዕዛዛቱም ፍትህ የራሱ ትዕዛዛት አለው፤ በዚህም ያልተዛነፈ መለኪያ የምትለኩበት ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ሀሳባችሁም አላማ አለው፣ ይህው አላማችሁም አካላዊ የሚሆን እና በመንግስቱ የሚኖር ይሆናል፤ አላማውም የሚዳኘው በመንፈሱ ሲተላለፍ ነው፡፡ የሰው አካልም የማግኔት ህግጋት ውጤት ነው፤ የሚመጣውም ከሁለንታ ነው ይህውም መለኮታዊ ህግ ይባላል፡፡ ማንም በሚወክለው ደቂቅነቱ መለኮታዊ መሆኑን የካደ፣ አባቱን የካደ ነው፣ ማነው ለልጆቹ ምርጡን የሚፈልግ እንዲሁ ማንም አባቱን የካደ የራሱን ዘላለማዊነት እንደካደ ነው፤ ምክንያቱም ማብቂያ በሌላቸው ገነቶች የራሳቸውን አይምሮ ያነባሉ፣ ማንም አባቱን ከካደ፣ ህልው ገነቶችም መግቢያቸውን ይከልክላሉ፣ ምንም ነገር በምድር ላይ ያደረጋችሁት

ከላይ ለስራቻሁን ውጤት ታገኛላቻሁ፤ እንዲሁም መንፈሳቻሁ ወደ የትም ቢጓዝ ህግ አንድ ነው፤ ትዕዛዛቱ ከላይም ሆነ ከታች ያሉት ተመሳሳይ ናቸው:: የሚለየው ቢኖር በቅጽበታት ህልውና ውስጥ ያለው ፍልስፍና ነው፣ ፍትሀቻሁ መንፈሳዊ የሆነ እና መሆንም ያለበት ይሄው ነው:: በህይወት ጣዕምና በዕውቀት ውስጥ መቆየት የማይችለው ቁሳዊነትስ ምንድን ነው:: የእያንዳንዱ መንፈስ ለየት ያለ ዕውነታ የሚኖረው ዘላለማዊነት ነው:: በሰውነት አካላችን የሚሰማንን ጊዜያዊ ህይወት አይነት ያልሆነ ነው:: የጠየቅነው ስጋዊ አካላችንም የሚሰጥህ ወይም የሚሰጥሽ ነው፤ ሰውነትን መስጠት ማንኛውንም ነገር እንደመስጠት አይደለም፤ ሰውነት ህያው የሆነ እና አካላዊ ቅርጽን ጨምሮ የሚጠይቅ ነው:: ተዋረሱም ለሁሉም ተመሳሳይ ነው:: ቁስ እና መንፈስ እኩል መብት አላቸው፣ ሁለቱም ይጠይቃሉ፣ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ህግጋት

ይጣመራሉ፣ በመንግስተ ሰማይም የቃል ኪዳን ታቦት በመባል ይታወቃሉ:: መንፈስን አለማዊ ማድረግም በዘፈቀደ የሚሆን አይደለም፣ በሀላፊነት የሚደረግ እንጂ፤ ተቃራኒውን ማለት ግን ራስን መናቅ ነው፤ ማንም ደግሞ ራሱን የናቀ፣ በውስጡ የሚገኘውን አባቱንም የናቀ ነው:: ፈጣሪያቹሁ ሁሉም ቦታ እንደሚገኝ አስባቹሁ አታውቁ ይሆን? ማሰብ በሚቻለው እና ማሰብ በማይቻልበት? በእውነት በአፋቹሁ ታውቃላቹሁ፣ ነገር ግን በዕውቀታቹሁ አይደለም፣ በራሳቹሁ ጥረት፣ በፊታቹሁ ላብ፣ በራሳቹሁ መልካምነት፣ እርሱን የሚፈልግ ያገኛል፣ ምክንያቱም በታላቁ ፍለጋ በለፋው ልክ ይሸለማል፣ ምክንያቱም በህልውናቹሁ ብዙ ነገሮችን ትፈልጋላቹሁ፤ እናም ለእናንተ ህይወት የሰጠውን አባታቹሁን ካልፈለጋቹሁ፣ ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም፣ ምስጋና ቢሶቹ በፍጹም ገብተው አያውቁም፣ ለትሁቶቹ ብቻ እንጂ፣ ለእነዚያ በህይወት ፍርድ

ውስጥ ለተጓዙት፤ ምክንያቱም እነዚያ ፍርዶች በራሳቸው በትሁቶች በመንግስቱ የተጠየቁ ናቸው፤ እያንዳንዱ የሚያልፍበት የህይወት ፍርድ በእያንዳንዷ ቅጽበት በእያንዳንዱ የሚያልፍበት የህይወት ፍርድ በእያንዳንዷ ቅጽበት በእያንዳንዷ ሰኮንድ የተጠየቀ እና የተሰጠ ነው፣ ይሄውም ሞታችሁን እና አሟሟታችሁን ሳይቀር እንኳ ትጠይቃላችሁ:: በራሳችሁ ፍርድም ታላቅ የሆነን ስብዕና ታሟሉ ዘንድ ትጠየቃላችሁ፣ ብቸኛውን ምክንያቱም ያለእርሱ መቼም ቢሆን ወደ መንግስተ ሰማይ ልትገቡ አትችሉም፣ እናንተም እንዲህ አይነት ስነምግባርን በምድር ትማሩት ዘንድ ጠየቃችሁ፤ መለኮታዊ ህግጋትም ተሰጧችሁ:: እነርሱም መቋሚያወች ናቸው፤ በእነርሱ ትዳኛላችሁ:: እስከ ፕላኔቲት ፍጻሜም እንዲህ ይሆናል:: የሰውም ልጅ መንፈስ እኔን በሚገባ ሊያውቀኝ አይችልም፣ ግን በህግጋቴ ስነ ምግባር ውስጥ አለመኖር ጨለምተኝነት ነው::

ምክንያቱም አባቴ ወደአለበት በፍጹም ልትገቡ አትችሉምና ነው:: ከብርሀን የምትርቁበት ጊዜም በውል አይታወቅም:: ቁጥሮችንም ለማንበብ ዳግመኛ መወለድ ይኖርባችኋል:: ይሄውም በደቂቅ ዝግመተ ለውጥ የሌለ ነው:: የምትጠይቁት ፍትህም የሚጀምረው አይምሯችሁ ሊፈጥር ከሚችለው ደቂቅ ነገር ነው:: ስለዚህም ደቂቋ፣ ትሁቱ በሁሉም መጀመሪያ ናቸው፣ በመንግስተ ሰማይም ሆነ በመለኮታዊ ፍርድ የመጀመሪያ እንዲሁም ከመለኮታዊው አባት ከጆቫ በፊት ናቸው:: እናም አይምሯችሁ ሊፈጥረው የሚችለው ደቂቁ ነገር ሀሳብ ነው:: ሁሌም እንደምታፈልቁት ያለ ተመሳሳይ የሆነ፣ በመንግስቱ እንደጠየቃችሁት ያለ፣ የሚሰማችሁ ግን እንደማይታያችሁ አይነት የሆነ:: ሁሉም ሀሳባችሁ በአካል ወደ ህዋ ይጓዛሉ፣ እናንተ እንዳላችሁ መብት አይነት አላቸው:: በነገሮች ትወለዱ ዘንድ ጠየቃችሁ እነርሱም እንዲሁ::

በጊዜ እና በቦታ ትኖሩ ዘንድ ጠየቃችሁ ሀሳቦቻችሁም እንዲሁ፣ ከላይ ያለው ከታች እንዳለው ሁሉ ተመሳሳይ ነው:: የጥያቄዎች ውርስም በሁሉም ዘንድ ተመሳሳይ ነው፤ የግዙፍ ነገሮች ጥያቄ እና የደቂቅ ነገሮች ጥያቄ፣ የህይወት ያላቸው ነገሮች ጥያቄ እና ህይወት የሌላቸው ነገሮች ጥያቄ፣ እናም ሁሉም ነገር ከአባት ይሰጣል፣ ምክንያቱም እርሱ መጨረሻ የለውም:: ሀሳባችሁ በህዋ ይጓዛል፣ የማይሰፈር ርቀት ልታሰሉት የማይቻላችሁን ርቀት፣ ሀሳባችሁም በመንግስቱ የታወቁ ናቸው፣ ይሄውም እንደ ጠፈር ዘር ሆነው ከእነርሱ ርቆ የእናንተው አለም በራሳችሁ ገነት ውስጥ ይወለዳል:: ይሄውም በነጻ ፈቃዱ ተጽፏል:: እያንዳንዱ የራሱን ገነት ይፈጥራል:: ምክንያቱም በደቂቅ ቅርጻችሁ ሁላችሁም የአባታችሁ ውርስ አለባችሁ:: ምንም  ይሁን አባት ያለው ሁሉ ልጆችም አላቸው:: በምድራዊ ወላጆች እንዳለው

ሁሉ ማለት ነው:: የዘር ባህርያቸው ለልጃቸው እንደሚተላለፈው:: ከላይ ያለው ከታች ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: አባታችሁ የሰጣችሁ ዘርም ፍልስፍና የሌለበትን የዋህነት ነበር ምክንያቱም የእናንተው ነጻ ፈቃድ ነው መምረጥ የሚችለው:: የሚኖሯችሁ ነገር ሁሉም መልካምነታችሁ ነው:: ምክንያቱም ሁሉም ነገር የሚፈጸመው በአንዱ ፊት ላብ ነው፣ በመንፈሳዊ ጥረትም፣ በአባት ፍጥረት ውስጥም አንዳች እንኳ ዋጋ የማያስከፍል የለም፤ ሁሉም ዋጋ ያለው እና የሚኖረው ነው:: ከእያንዳንዱ መንፈሳዊ መልካምነት ውጪ ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት የሚቻለው የለም፣ አለማዊ ምቾትም በገነት አንድ እንኳ ዋጋ የለውም:: በአለም ላይ የተገኘው ምቾትም ተደስታችሁ ያለፋችሁበት ሽልማት ነው:: እናም ይሄን ምክንያት አድርጎ ነው የተጻፈ:: ማንኛውም ቁሳዊ ደስታ በገነት ላይ አንዳች እንዷ መልካምነት የሌለው ነው:: እናም ከሁሉም ቢያንስ ቢያንስ

እነዚህ ፌሽታዎች የአባትን ትዕዛዛት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገቡ ፍልስፍናዎች ውጤት መሆናቸው ነው:: እነዚህ ፍልስፍናዎች ቀናቸው ይቆጠራል ምክንያቱም ፈጣሪ ይሰጣል ይነሳልምና ነው:: ይህ ቁሳዊ ፍልስፍና ገና ስር ሳይሰድ ይቀጫል:: ይሄውም ሁሉም የራሱ ጊዜ ስላለው ነው ምክንያቱም ደግሞ ሁሉም ነገር ከአባት ትዕዛዛት ጋር አንፃራዊነት ስላለው ነው፤ በራሳቸሁ የህይወት ፍርድ ላይ የምትጠይቁት አይነት አንጻራዊነት:: የህይወታቸሁ ዘየ መውደቅ ማለት የራሳቸሁን ቀንበር ጥላቸኋል ማለት ነው፤ ለትሁቱም ትልቅ ክስተት ይሆናል፣ እንዲሁም ለተበዘበዘው እና ለተናቀው ጭምር:: ሁሉም የሰው ልጅ በአምላክ ፊት እኩል እስከሆነ ድረስ፣ ማንም ሀብታምም ሆነ ድሀ ሆኖ አልተወለደም፣ እንዲህ አይነት ነገሮች የተፈጠሩት በምኞት መንፈስ ነው፣ የአሁን ህይወታቸውን ብቻ የሚኖሩት፣ እኒህም በሰው የእድገት ደረጃ ኋላቀር

መንፈሶቹ ናቸው:: በዚህ የአጭር ጊዜ አስተሳሰባቸውም ስለ ዘላለማዊነት አንዳች እንኳ ሳያደርጉ አለምን ተቆጣጥረዋል:: እነዚህ ሁሉ ሰይጣናት በራሷ በአለም ይዳኛሉ፤ ምክንያቱም ማንም ነብሱን ማስወቀስ አይፈልግም፣ የአምላክ በግ ዶግማ ብርሀን አለምን ያድሳታል፣ ምክንያቱም በመንግስተ ሰማይ የተጻፈው እንደዚያ ስለሆነ፣ ይህቺ ምድራዊ አለም እያደረገች ያለው ግን ከተነገራት ተጻራሪውን ነው:: በክፍለ ዘመናት ሁሉም መለኮታዊ ትዕዛዛቴ ሲነገር ኑሯል፣ ትሁቶች የመጀመሪያ ናቸው:: በነገሮች ደረጃ ላይ ሁሉ፣ እናንተስ በሰማያዊ ትዕዛዛቴ ምን አደረጋቸሁ? የኔ ትህትና በነገሮች ሁሉ ላይ የመጀመሪያ ቢሆንም አለምን ገዛ? በእውነት ይሄ አልሆነም፣ ምክንያቱም ሁሉም ትሁቶች ተንቀዋል፣ እነሱ ከስነምግባር ከወጡት ከሀብታሞች ተርታ ሊሰለፉ አይቸሉም:: እንዲሁስ ደግሞ እንዲህ አይነት መደቦችን ትፈጥሩ ዘንድ

ማን መብት ሰጣቻሁ? በቅዱሳን ጽሁፎቼ ውስጥ አለ ይሆን? እውነት እላችኋለሁ እናንተ እርባና ቢስ ሰይጣኖች ፈጣሪ ያልተከለው እያንዳንዱ የፍልስፍና ዛፍ ከስሩ ተነቅሎ ይጣላል፤ ሌሎችም ህያው ዝግመተ ለውጦች እንዲህ ይሆናሉ:: ማንስ ደግሞ ፈጠራችሁ እንዲሁም ንጉስ ያደረጋችሁስ? አባት ብቻ የንጉሶች ንጉስ እንደሆነ ታውቃላችሁን? እናም ንጉስ የሚለው ማዕረግ ለዚህ አለም የተገባ ሳይሆን ለሰማያዊው አለም የተገባ ነው፤ ሰይጣንም የመናፍስቶች ንጉስ ይባላል፣ መለኮታዊ ህግጋትም ከምንም ነገር በላይ ትህትናን ያስተምራሉ እንጂ ራስን ያነግስ ዘንድ አያስተምሩም:: እውነት እላችኋለሁ እናንተ የተረገማችሁ የሰይጣን ባለሟሎች፣ ማንኛችሁም ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም፤ ከእናንተ ጋርም ልጆቻችሁ እስከ ሶስት ትውልድ ድረስ አይገቡም፤ ምክንያቱም በአባት ጆቫ ህልው ሁለንታ ውስጥ እያንዳንዱ ዘር ይተላለፋል፤ ምንም ነገር ዋጋ ቢስ

አይሆንም በደቂቅ የጊዜ ሰኮንድም ቢሆን፣ ምክንያቱም በአንዲት ሰከንድ ወይም ባነሰች መተላለፍ እንኳ ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም:: የተረገማቸሁ የአለም ንጉሳን የልጆቻቸሁ ንጹህነት ይረግማቸኋል፤ ምክንያቱም በእናንተ ምክንያት ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት አይቸሉም፣ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር የእናንተን ርጉም ፍልስፍና ሲያገለግሉ የነበሩት እያንዳንዱ ወንድ እና ሴት ጭምር አይገቡም:: የሰይጣን ባለሟል የሆነ አንድ እንኳ ወደ መንግስቱ ሊገባ አይቻለውም:: ምክንያቱም በመንግስቱ ዘንድ የስራ ዋጋ ብቻ ነው የሚታወቀው:: ይሄውም የሁለንታ ፍልስፍና የሆነው ትሁቶች እና ታማኞች የሚጠየቁት፣ እነዚያ የምድር ንጉሶች እና ንጉስ የነበሩት ግን ዋጋ ቢስ አሳሳች መናፍስቶች ናቸው:: በእነዚህ መንፈስ ውስጥ የግዙፉ ህዋ በሌሎች ነገሮች ተጽዕኖ የወደቁ ናቸው፣ ጨለማን የሚገፍ የዕውቀት ጣዕም ሳይሆን የቁሳዊ

አብረቅራቂነት መኖር የማረካቸው፡፡ እንዲሁም በአንዳች አለም ላይ ነግሶ ያልነበረ ሰይጣን የለም፡፡ ይህ ፍልስፍናም የሚመራው በራሱ በሰይጣን ነው፣ ልክ አመጻውን በጀመረበት ቅጽበት እና ከእርሱ ጋር አብረው ያመጹት ሌጌዎኖቹ ጭምር፡፡ በመንጋ ይሆን ዘንድ የጠየቀው የሰው ልጅ መንፈስ ሁሉ፡፡ በንጉስ የምትመራ ሀገር ሁሎችም የሰይጣን ሌጌዎኖች ናቸው፡፡ ሁላችሁም ከገነት ትባረራላችሁ፣ ሰይጣን ከዚያ እንደተባረረው ሁሉ፤ በገነት በመሆንም መንፈሶች የሌሎችን ፍጥረታት ልማድ ይወስዳሉ፣ ይሄውም በመሀከላችሁ እንዳለው ሁሉ ነው፡፡ ከላይ ያለውም ከታች እንዳለው ያው ነው፡፡ ሰይጣንን የሚያስተጋቡትም ሀይማኖተኞች፣ ሀብታሞች፣ ንጉሶች እንዲሁም የሀይልን ፍልስፍና  በሚፈጥሩ ርጉማን ዘንድ ተሰራጭቷል፤ ነገር ግን የትኛውም ሰይጣን አይጸናም፡፡ የመለኮታዊው አባት ህያው ቃል ሁሉንም ነገር ያጠራል፣ ሁሉንም ነገር ያድሰዋል፤

የጥንቱን አለም በሙሴ ህግጋት በመቀጠልም በክርስትና ዶግማ እንዳደሰው ሁሉ፣ አሁን ደግሞ በአምላክ በግ ዶግማ ያድሰዋል:: ለሁለንታው ሁሉ ፈጣሪ የስጋ አለምን በህያው ቃሉ ከማደስ የቀለለ ነገር የለም:: ያ ቃል ከሰማይ ቅጽበታት በፊት ብርሀን ይሁን ያለው ብርሀንም ያደረገው፣ ያ ተመሳሳይ ቃል እያንዳንዱን ቅዱሳን ጽሁፎች የፈጠረው፣ ያ ትዕዛዛቱን የሰጣችሁ ተመሳሳይ ቃል፣ በዕውቀታችሁ በሰውነት ህግ የሚዳኛችሁ ተመሳሳይ ቃል:: ምክንያቱም እያንዳንዱ መንፈስ በዚያ መልኩ ተጠይቋል:: በመጨረሻው የፍርድ ቀን ለፍርድ ይቀርቡ ዘንድ ጠይቀዋል፣ በእያንዳንዷ የህይወት ቅጽበት ይፋረዱ ዘንድ እንደጠየቁት ሁሉ፣ ቅዱሳን መጽሀፎቹን ለመተርጎም ከሚያስቸግራችሁ ጀምሮ:: ሁሉም ነገር በአጠቃላይ ሁሉም ነገር በእናንተው የተጠየቀ ነው:: ይቺ ትንሿ የአምላክ በግ ትንታኔ ሳይንስ ሳትቀር በእናንተው የተጠየቀች ናት::

ይሄም ለእናንተ የማይታያችሁ ነገር እንኳ ከመንግስተ ሰማይ እንደምትቆጣጠሩ ግንዛቤውን ይሰጣችኋል:: የማይታወቅ ስሜታችሁ፤ ፍትህም:- ለአስተሳሰባችሁ፣ ለሀሳባችሁ፣ ለአላማችሁ ነው፣ በመንግስቱም እናንተው ራሳችሁ የጠየቃችሁት ነው:: መሰረታችሁንም ትዘነጉት ዘንድ የጠየቃችሁት ነው፣ እንዴት እና ለምን እንደተፈጠራችሁ:: ነገር ግን ሁሉን ነገር ማወቅ አለባችሁ፣ ምክንያቱም በምድር ላይ የአምላክ በግ ብርሀንን ታዩት ዘንድ ጠይቃችኋል:: ከዕውቀት ትስማሙ ዘንድ ጠይቃችኋል፣ አዲስ ዶግማን ጠይቃችኋል፤ ይህ ዶግማም ሳታስቡት ይመጣ ዘንድ ጠይቃችኋል፤ የአምላክ በግ ዶግማ፤ ከረጅም ጊዜ በፊት ታውቆ በሆነ ነበር:: አለማመናችሁ እና የሀይማኖት አለትን ቁሳዊ ማድረጋችሁ እውነታውን ከእናንተ ሰውረው እነሱ የበጉን ጥቅል ይዘዋል፣ የመጀመሪያዎቹ ጥቅሎች በእጃቸው ተቀመጠ፣ ምክንያቱም

እነርሱ ተፋርደዋል እያንዳንዱ መንፈስም ይፋረዳል እነዚያ ሰይጣናት እነርሱ እንኳ የማያምኑበትን እምነት ያስተምራሉ:: የእውነት እውቀት ይኖራቸው ዘንድ የመጀመሪያዎቹ ይሆኑ ዘንድ ተጠይቀዋል፤ እናም ተሰጥቷቸዋል፤ እውነትን የሚደብቁት ግን በልባቸው ባበቀሉት የራስ ወዳድነት አለት ነው:: እነሱ ታናሽ አማኞች ናቸው:: በቁሳዊ ውበት የተማረኩ ናቸው፤ የፈርኦን ዘር፤ ሰውን እንድታመልኩት የሚመራችሁ፣ እውነት እላችኋለሁ የውበት ሰይጣኖች አንዲት ነጠላ ቃሌን አሳስታችሁ ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም፤ አንድ ነጠላ ራስ ወዳድ አለት እንኳ መግባት አይችልም፤ በዚህ ትውልድ እና በሚመጣው ሁሉ የተረገማችሁ ትሆናላችሁ በእናንተ ሰይጣኖች ምክንያት ይሄ የሰው ልጅ ወደ መንግስቱ አይገባም:: ምክንያቱም ሁሉም ሁለተኞቹ በመተላለፌ ጊዜ የኖሩ ናቸው:: የአንዲት ሰኮንድ ወይም ያነሰች ጊዜ መተላለፍ

ወደ መንግስተ ሰማያት ላለመግባት ምክንያት ይሆናል:: እውነታውንም ከአለም ከሰወራቸሁት የሰውን ልጅ ሁሉ ከመንግስቱ አራቃቸሁት ማለት ነው:: ምክንያቱም ስህተቱን የበለጠ አራዘማቸሁት፣ በስህተት ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ ሰኮንድም ይበልጥ ትልቅ ነው:: እያንዳንዱ በመተላለፍ ያለፈ ሰዶንድ የገነት በር የተዘጋበት ነው:: ሁላቸሁም ሰኮንዶቸን ደምራቸሁ ደቂቃ፣ ሰዐት፣ ቀን፣ ሳምንት፣ አመት በአጠቃላይ የዕድሜ ዘመናቸሁን ሰኮንድ ታውቃላቸሁ:: እያንዳንዱ ስሌትም ከአስራ ሁለት አመት ጀምሮ ያለው ይሆናል፣ ከዛ ዕድሜ በፊት፣ እያንዳንዱ መንፈስ በአምላክ ዘንድ ንጹህ ነው:: እንዲሁም ማንም ከንጹሀኖቼ  አንዱን በቃልም ሆነ በተግባር ለአንዲትም ሰኮንድ ሆነ ከዚያ ላነሰ ጊዜ ቢበድል ወደ መንግስተ ሰማይ አይገቡም ምክንያቱም እነሱ በንጹህነታቸው ጊዜ መበደላቸውን በመንግስቱ ፊት አቅርበዋል፣ በዚህ

ምክንያትም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል በእናንተ ላይ ይደረግባችሁ ዘንድ የማትወዱትን ነገር በሌሎች ላይ አታድርጉ፡፡ በዚህ ምክንያት መጥፎ አባትም ሆነ እናት ወይም ደግሞ የእንጀራ አባትም ሆነ የእንጀራ እናት ወይንም አሳዳጊ ወንድም ሆነ ሴት ወደ መንግስቱ ሊገባ አይቻለውም፡፡ እጣ ፈንታቸው በንጹሀኖቹ ፍትህ ላይ ይወሰናል፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ትንሽ በመንግስተ ሰማያት ትልቅ ነው፡፡ እያንዳንዱ ትሁት ሰው ከአባት ፊት የመጀመሪያ እንደሆነ አልተማራችሁምን? ይህ ማለት በአባት ጆሮ ፍትህ ዘንድ እያንዳንዱ ደቂቅ የመጀመሪያ  ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት የእናንተ መንፈስ በመንግስቱ ፊት የመጀመሪያ አይሆንም፡፡ የመጀመሪያ የሚሆኑት የእናንተ መንፈስ በምድር ላይ የናቃቸው ይሆናሉ፡፡ መንፈሳችሁ የመጀመሪያ ይሆን ዘንድ መጠየቅ አይችልም፣ ምክንያቱም ከምንም ነገር በላይ ትሁት ትሆኑ ዘንድ ታዝዛችኋል፣ በመጨረሻ የሚሆነው ትሁቱ ነው፤

የራሱን ጥቅም አያስቀድምም፡፡ እውነት እላችኋለሁ ጥቅምን ለራሱ የሚያስቀድም ወደ መንግስተ ሰማይ መግባት አይቻለውም፣ ይህ ያልተገባ ጥቅም ለአንዲት ሰኮንድ ወይም ላነሰ ጊዜ ቢቆይ እንኳ እናም እያንዳንዱ ደካማ አስተሳሰብ ለተመሳሳይ ጊዜ ያህል ያደረገ ቢኖር እንኳ ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት አይቻልም፡፡ የዚህ የሰው ልጅ ውድቀትም ከሀሰት እና ከአለማዊ ሀሳብ የመነጨ ነው ይሄውም በሀሰተኛ የሀይማኖት አለት የተተከለ ነው፡፡ ይህ ብልግናም ለብዙ ክፍለ ዘመናት ለጊዜያዊ ፍላጐት ማሟያ ብቻ በእምነት ስም ተነግዶበታል፡፡ እርሷም ትህትናን ግንዛቤ ውስጥ አላስገባችም፣ ትሁት ራሱን በቅንጦት አይከብም፣ ራሱን አይዋሽም፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ትሁት አጠያያቂ ዝና ፈላጊዎች ባለፉበት ያለፈ ነው፣ እያንዳንዱ አለማዊ ኋላ ቀር መንፈስ ነው ተስፋውን በደቂቃ አሁን ላይ መስርቷልና፣ ከዚህም በበለጠ ለመንፈስ

ህግጋት ጭፍኖች ናቸው፤ ይሄው አይነት ባህርይም በጳጳሳት ዘንድ ያለው ነው፣ እነርሱ የብልግናው መሪ ናቸው:: እነዚህ ፍጡራን በመንግስቱ ዘንድ አይታወቁም፤ ምክንያቱም ከትሁቶች እና ታማኞች በቀር ማንም አልገባ:: እንዲሁም እያንዳንዱ ሀይማኖት አይታወቅም እንዲሁም የእናንተው ፕላኔት አትታወቅም:: ይሄውም ማብቂያ በሌለው ህግ ምክንያት ነው፤ አንደኛውም ይህ ሁለንታ ማብቂያ የሌለው ነው፤ ስለዚህ ማብቂያ በሌለው ነገር ውስጥ እያንዳንዱ ቅዠት እውነት ይሆናል ሌላው ደግሞ እያንዳንዱ የራሱን ገነት ይሰራል:: በዚህ መልኩም እነዚያ ጳጳሳት እና የእነርሱ ተከታይ በቁሳዊ መዋብ ፍልስፍናቸው የራሳቸውን አለም በዚያ ፍልስፍና ፈጥረዋል:: ምክንያቱም ደግሞ እያንዳንዱ አለም በገነት የተከበበ ነው እንዲሁም እያንዳንዱ የራሱን ገነት ይፈጥራል:: ቁሳዊ መዋብም በመለኮታዊ አባት ያልተተከለ ዛፍ ነው እናም በመንግስቱ አይታወቅም:: የትኛውም

ዶግማ፣ ሳይንስ ወይንም ቤተ እምነት ይሁን ትህትና የሌለበት ከሆነ አይታወቅም ምክንያቱም በዕውነት ብያቾኋለሁ ይቾ ፕላኔት በትሁቱ መገዛት አለባት ምክንያቱም እነርሱ በመንግስቴ የመጀመሪያዎቹ ናቸው:: በላይ የመጀመሪያዎቹ ስለሆኑ ከታችም እንዲሁ መሆን አለባቸው:: ይሁን እንጂ በተቃራኒው ነው እየሆነ ያለው:: አለሙ እየተገዛ ያለው በመንግስቱ ይሆኑ ዘንድ ባልጠየቁት ነው:: የጨለማው መንፈስ እየገዛቸሁ ነው:: ምክንያቱም በቦታቸው ዘንድ በብርሀን ስም አያደርጉትም፣ በንግግራቸውም እኔን አይጠቅሱም፣ አላማቸው ፈጣሪያቸው አይደለም፣ አጭር ጊዜ እንጂ ይሄውም ከዘላለማዊነት በፊት የእስትንፋስ ያህል ቆይታ ያለው፣ አይምሯቸውን አነበብኩ ስሌታቸውን አየሁ፤ ምክንያቱም ሁሉም ቦታ አለሁ፣ የእነርሱን አለም በጨለማ እንደገነቡት ተመለከትሁ:: እውነት እላቾኋለሁ እናንተ ኩራተኛ እና እርባና

ቢስ መሪዎች ማናችሁም አትፀኑም፡፡ ማንም ትዕዛዛቴን ግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ አይጸናም፡፡ ትሁቱ አለምን ከጅማሬ አንስቶ ገዝቶ ቢሆን ኑሮ ይህ አለም ምንም አይነት ፍርድ ባላስፈለገው ነበር፡፡ ፍርድን የፈጠሩት ተላላፊዎች ናቸው፣ አንድስ እንኳ ተላላፊም ወደ አባት መንግስት አይገባም፡፡ ህጉም በእናንተ በራሳችሁ ያለ ነው፣ ሁሌም እንዲዚያ ነበር፣ ማሰብ ፈለጋችሁ እናም የራሳችሁን ፍርድ ፈጠራችሁ፤ ቁስ እና መንፈስ በየዘርፍ ህጋቸው ያስባሉ፡፡ ያለውርስ የቀረ እስከሌለ ድረስ ሁሉም እኩል መብት አለው፡፡ ማንም በአባቱ ፊት ታናሽ አይደለም፡፡ እኒህ ሁሉ መብቶች ማሰብ በሚቻልበት መልኩ ተቀምጠዋል፣ በአለም የምታዩት ነገር ሁሉ የጠየቃችሁት ጥያቄወቻችሁንም የታዘባችሁበት ነው፤ ምክንያቱም ወደ ፕላኔታዊ ኑሮ ከመምጣት በፊት፡፡ ከወደፊት ነገሮች ላይ የተደረጉ ቃልኪዳኖች ከዚህ ቀደም የተደረጉ ናቸው

እንዲሁም በህልውናችሁ የምታዩ ት ሁሉም ነገር በመለኮታዊ ቃል ኪዳኔ በራሳችሁ የተጠየቁ ናቸው:: ለዚህ ነው በህልው የአባት ጆቫ ሁለንታ ውስጥ ቁስ እና መንፈስ ፍርድን የመጠየቅ መብት ያላቸው::እንደዚያ ባይሆን ኑሮ ትክክለኛ ፍርድ ባልኖረ ነበር:: በእያንዳንዱ መብትም ሚዛናዊነት በሌለ ነበር:: የአባት ፍትህ አንድ ብቻ ሆኖ ሳለ ማብቂያ በሌለው መልኩ ይገለጻል:: ምክንያቱም ከእርሱ የሆነ ሁሉ ገደብ የለውም:: እያንዳንዱ ፍትህ የሚወለደው በፍጥረታት በሚደረገው ድርጊት ነው:: ይህም የህይወት ጣዕም በአንድ ህልውና ውስጥ የሚማሩት አንድ እውቀት ነው፣ ነጻ ፍላጎቱን በማገናዘብ መንፈስ ዕውቀትን ከማግኘት አንጻር እኩል አይገስግስም፣ አንዳንዶች መጀመሪያ ናቸው በመቀጠልም ሌሎች፣ ይህ ህግ የሚገልጸው በመካከላችሁ ያለውን አካላዊ አለመመጣጠን ነው:: እያንዳንዱ እውቀት ወይንም የህይወት ጣዕም በእናንተ የሚቀጥል

ይሆናል። ነገር ግን ሁሉም ነገር ማብቂያ በሌለው ሰመዘን አንጻራዊ ይሆናል ባህርያቸሁን እና የኑሯቸሁን አቅም በራሳቸሁ ትፈጥራላቸሁ ባህርያቸሁም በአስተሳሰብ ፍልስፍናቸሁ የሚሰጥ ይሆናል እንዲሁም የመንፈሳዊነት ዋጋቸሁ ደግሞ በመንግስተ ሰማያት ይሰጣል። ትልቅ ዋጋ የሚገኘውም በትህትና ነው በማስቀጠልም በደስታ እና በስራ ነው። እነሆም በሰማዩ መንግስት ዘንድ ኮሚዩኒዝም ይሟላል፣ ሰማያዊ ኮሚዩኒዝም ከልጅ ፍልስፍና ጋር፣ በህይወት ደስታን የማይኮተኩት እርሱ ወደ መንግስተ ሰማይ መግባት አይቻለውም። በባህርይው ጅልነት ያለበትም መግባት አይቻለውም ምንም እንኳ ጅልነቱም ሆነ ንዴቱ ለአንዲት ሰኮንድም ሆነ ላነሰ ጊዜ ብትቆይ እንኳ ማለት ነው። ሁላቸሁም በህይወታቸሁ ደስተኛ ለመሆን በመንግስተ ሰማይ ቃል ገብታቸኋል፣ ገነትን ራሷን ለመድገም፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆናቸሁ ደስተኛ

ለመሆን ቃል ገብታችኋል፣ ገነትን ራሷን ለመድገም፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆናችሁ ደስተኛ ለመሆን ቃል ገብቷችኋል:: ጅል ለመሆን አልጠየቃችሁም፣ ምክንያቱም ያ በመንግስቱ እንደማይታወቅ ታውቃላችሁና ነው:: እንዲሁም ጅል በመሆን መግባት እንደማይቻል ታውቃላችሁ:: በህልውናችሁ በተደጋጋሚ ተናዳጅ የምትሆኑ ከሆነ የዚህ ምክንያት ያ ሰው የመረጠው የተዛባ የህይወት ዘየ ነው:: እናም የዚህ አኗኗር ዘየ ፈጣሪ በፍርድ ጊዜ ዋጋቸውን ይከፍላሉ:: ምክንያቱም እንደዚያ ጠይቀዋልና ነው:: እንዲሁም ለእነርሱ ይሰጣቸዋል፣ እነዚያን በዝባዥ ካፒታሊዝምን የፈጠሩ ሰይጣኖችን በተመለከተ መለኮታዊ ፍትህ በእነርሱ ላይ ይወርዳል:: እነዚህ የምኞት እና የሀይለኝነት ሰይጣናት የዘላለማዊ አባት መለኮታዊ ህግጋቱን በዚህ አለም ለማስረጽ ቃል ገብተው የራሳቸው ጨካኝ አምባገነኖች ላለመሆን ነበር::

ምክንያቱም የዚህ ህይወት ዘየ ውጤት የጥሩ እና የምቾት ሳይንስ ነው:: ይሄም የአለም ቀንበር ነው:: ከበስተመጨረሻ እየቀረበ ቀምበር:: ይሄውም የአዲሱ ጊዜ ጅማሮ መቅረብ፣ አዲስ አለም በአዲስ ጊዜ፣ አዲስ ስነምግባር ከአዲስ እጣፈንታ ጋር:: ፈጣሪ ሁሉን ነገር እንደሚያድስ አልተማራችሁምን? የመጨረሻው ፍርድ የሚነሳው በአምላክ በግ ዶግማ ነው፣ የሚያም ፍጻሜ፣ ምክንያቱም እያንዳንዱን የአባት ህግ መተላለፍ ህመም ያስከትላል:: ልክ በህልውናችሁ ውስጥ እንደምታስተናግዱት፣ ኢ ፍትሀዊነት ማለት ነው፤ ከህይወት ዘየ የተወለደ ኢ ፍትሀዊነት በመለኮታዊ አባት ዘንድ እና በመንግስቱ የማይታወቅ::

በአልፋ እና ኦሜጋ ተጻፈ



ለዚህ ትውልድ የሆነ የአምላክ ብልህ ፍርድ

# ምን ይመጣል

ምን ይመጣል፣ የሚወሰነው በእያንዳንዱ ነው፣ የተጻፈውም፣ እያንዳንዱ በስራው ይዳኛል፣ የአምላክ መለኮታዊ ፍርድም ከአስራሁለት አመት በላይ ሀሳብ በሀሳብ ያካትታል፣ እነዚያ ህጻናት ብቻ ናቸው መለኮታዊ ፍርድን የማይጋፈጡ፣ የአምላክ መለኮታዊ ፍርድም የሚመረምረው እና የተፈተኑትን ጎልማሶቸ ነው፣ በሁለተኛነት የታሰበው ከህልውና ጋር እኩል ነው፣ ይሄውም እንደታሰበበት ሁሉ ብርሀናማ ህልውናን ማግኘት ወይም ብርሀናማ ህልውናን ማጣት፣ እነዚህም አምላክ ማብቂያ የሌለው ስለመሆኑ ነው፣ ለዘላለማዊው ለእርሱ የምናደርገው የደቂቃ አእምሯዊ ጥረት ሙሉ ህልውናን ይሰጣል፡፡

በአልፋ እና ኦሜጋ



ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የኖረው ራዕይ እንዴት ተጀመረ

አልፋና ኦሜጋ:- ተመልከቱ፣ እኔ እንደማንኛውም ነበርኩ፤ ሁሌም እንደማንኛውም ነበርኩ፣ በዚህ ትዕዛዛቱን አሟላለሁ:: አባትም እንዲህ አለኝ፣ እስከ አሁን ድረስ በያዝኳት ማስተዋሻ ላይ እንድጽፍ አደረገኝ፣ መልዕክት ሰጠኝ፣ እንድጽፍ አደረገኝ፣

አስታውሳለሁ በውስጡም እንዲህ ይላል:: ልጄ ምረጥ፣ አምላክን ማገልገል ትፈልጋለህ ወይንስ አለማዊ ህይወትህን መቀጠል? ይህ ምርጫ ነበር፣ ምክንያቱም በህይወት ውስጥ ነጻ ፍቃድን ጠይቃቸኋል፣ እንደማንኛውም ሁሉ እርሱም ለማሰቢያ ሶስት ደቂቃ ሰጠኝ፣ መስተዋል ያለበት ነገር እመርጥ ዘንድ አማራጭ ሰጠኝ፣ በመቀጠልም እንዲህ አቀረብኩ፤ ምላሼ በመንፈሳዊ መልዕክት ያለጸሀይ፣ በተጻፈ እንደተጠየቀ ተጽፎ፣ እያንዳንዷ ስሜትም ከአምላክ የተጠየቀች ናት፣ እንዲህም አልኩ:- አባት ጆቫ እከተልሀለሁ፣ ምክንያቱም ከሰው የሆነው ዘላለማዊ አይደለም፣ ዘላለማዊ የሆነውን እከተል ዘንድ እመርጣለሁ::

ወንድም: ግን ትንሽ፣ በዚያ ጊዜ ትንሽ ነበርክ?

ደራሲ: አወ ነበርኩ

ወንድም: ሰባት አመት, እና አሁንም ታስታውሰዋለህ?

ደራሲ: አወ፣ አወ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የያዝኳቸው ማስታወሻወችና ወረቀቶች በጊዜ

ብዛት ምክንያት ቢጫ ሆነዋል፣ በሳጥን ማስቀመጥ ይኖርብኛል፣ ወደዚያው ነው ያለው:: በመቀጠልም አባት እንደነገረኝ፣ አወ ልጄ አውቄዋለሁ፣ ነገር ግን ፈተናውን ማለፍ ይገባሀል:: ምንም እንኳ ዘላለማዊው ቢያውቀውም ፈተናውን ማለፍ ይገባሀል፤ እርሱን ካላለፍህ ምንም አይነት ልምድ አይኖርህም::

እህት: ግን እንደዚያ በሚያስገርም ነገር እንዲሁ አገኘህ: በቃ ልክ እንደዛ፣ ድንገት መረጠህ?

ደራሲ: አወ፣ ይህን እነግርሻለሁ፣ ማንኛውም በምናብ ሊታይ የሚችል ነገር ሁሉ ከአምላክ የተጠየቀ ነው፣ ማንም አንድ ነገር ለመፍጠር እንደሚጠይቅ ሁሉ፣ እኔም ራዕይ እንገልጥ ዘንድ ጠየቅሁ፣ እያንዳንዱ በህግ ያለ ከአምላክ የተጠየቀ ነው::

መነሻ ገጽ

የእግዚአብሄር ነገር ለማንም ለብቻው የተሰጠ አይደለም

ሳይንስ፣ ስነምግባር፣ ፊዚዮሎጂ፣ የጠፈር ፍልስፍና፣ መለኮታዊ ፍትህ

ምድር ሁሉ፣ ለእግዚአብሄር እልል በሉ

መዝሙር 100

የሁለንታው ሁሉ ፈጣሪ በመንፈሳዊ መልዕክቶቹ ከሁሉም ጋር በቀጥታ ይገናኛል::

ወደ ትርጓሜ እቅድ እንኳን ደህና መጣችሁ

ይህን የመንፈሳዊ መልዕክት ትርጓሜ ስናቀርብላችሁ ገና በአልፋ ወይም በጅማሬ ደረጃው ነው::

ይህ መልዕክት ተጽፎ የነበረው በስፓኒሽኛ ነው::

የአለም አባላቶችም ትርጓሜውን ማብቃት አለባቸው በዚህ መልኩም ጥሩ መተርጎም የቻሉት ይመረጣሉ::

መጽሀፍቶችንም በአንድ ክሊክ ማውረድ ይችላሉ

የሁለንታ ሳይንስ፣ መንፈሳዊ መልዕክት ያለው ጽሁፍ ሲሆን፣ ምሳሌውም የአምላክ በግ ነው::

አልፋና ኦሜጋ የግዙፍ መንፈሳዊ መልዕክቶች የጻፈው ጿራሲ ነው:: እስከ 1978 እኤአ በቺሊ እና በፔሩ 4000 ጥቅሎችን ጽፏል::

ይህ የሁለንታ ሳይንስ፣ የሁሉንም ነገር መነሻ የሚገልጽ እና የሚገልጽ እና የሚመጣውንም ነገር የሚያበስር ነው::

ራዕዩ ለክፍለ ዘመናት ሲጠበቅ ኑሯል

ይህ ራዕይ በመላው አለም ይሰራጫል፣ እንዲሁም ወደ ሁሉም የአለም ቋንቋዎች ይተረጎማል፣ እንዲሁም በትርጓሜው የማይሳተፍ አንዳች እንኳ ተርጓሚ የለም:: ምክንያቱም በእያንዳንዷ ሆሄ ትርጓሜ ብርሀን ይሆናል

ይሄም የማህተሙ ራዕይ ነው፣ እናም በአባት የተላከ አንድ ብቻ ይላል፣ የአምላክ በግ ጥቅሎችን መጻፍ ትችላለህ::

ሁሉም የአምላክ በግ ራዕዮች በቀጭን የወረቀት ጥቅሎች እና በካርቶን ላይ ይሆናሉ እናም ለአለም

የተሰጡት መንፈሳዊ ጽሁፎች ይሟላሉ፣ ጥቅሎቹም በመንፈሳዊ መጽሀፍት ተልዕኮ ውስጥ የሚቀመጡ ይሆናል እንዲሁም ለያዙት እውቀት ፍጻሜ የለውም ስለሚመጣው እና ስለ ሁለንታ ሳይንስ ለማንበብ እባክዎ



ይህ መለኮታዊ ራዕይም፣ በራዕይ መጽሀፍ ውስጥ እንደ ጥቅሉ እና እንደ በግ ሆኖ ተነግሯል (ምዕራፍ 5)

# የሁለንታ ሳይንስ









ይህ መለኮታዊ ራዕይም፣ በራዕይ መጽሀፍ ውስጥ እንደ ጥቅሉ እና እንደ በግ ሆኖ ተነግሯል (ምዕራፍ 5)

https://www.alfayomega.com/ ብለው ይጎብኙ

https://www.facebook.com/RevelacionAlfayOmega/